ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 28 ጥቅምት 15/2018 ዓ.ም

## በውስጥ ገጾች

በኮሚሽኑ የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ዘርፍ የ2018 በጀት 1ኛ ሩብ አመት እቅድ አፈፃፀምን ከክልል ኮሚሽኖች ጋር በሸርቹዋል ገመገመ
ገጽ 3

የስነ-ምግባር ጥሰት በፈፀሙ 20 አመራርና ሰራተኞች ላይ እርምጃ ተወሰደ
ገጽ 5

የሥራ አመራር ቦርድ ድርሻ እና የጥቅም ግጭት ተጋላጭነት
ገጽ 9

## ኮሚሽኑ 18ኛው ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀን አከበረ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን 18ኛው ብሔራዊ የሠንደቅ ዓላማ ቀንን "ሠንደቅ ዓላማችን፣ ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ሕዳሴ" በሚል መሪ ሀሳብ ከኮሚሽኑ ስራ ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ጋር አክብሯል፡፡

የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ የታተመ የሀገራዊ አንድነትና ነፃነት መገለጫ ታላቅ የብሔራዊ ኩራት አርማ እንደመሆኑ በሁሉም የሀገሪቷ ክፍል በድምቀት ተከብሯል፡፡

ግላዊ ጥቅምን መሰረት ያደረጉ ፖለቲከኞች፤ እታገልልሃለሁ የሚሉት ሕዝብ ፍላጎት ቢሳካም እንኳን፤ እነርሱ ስልጣን እስካልያዙና ሃብት እስካልተቀራመቱ ድረስ ተሳክቷል ብለዉ አያምኑም፡፡ ሕዝብ በላ የሚሉት እነሱ ሲበሉ፤ ሕዝብ አጣ የሚሉት እነሱ ሲያጡ ነዉ፡፡ እነሱ የሕዝብ አካል ሳይሆኑ የሕዝብ መለኪያ "ቴርሞ ሜትሮች" ናቸዉ፡፡

- ከጠ/ሚ አብይ አህመድ መጽሀፍ፣ የመደመር መንግሥት ገጽ - 282

# ኮሚሽኑ ከአፍሪካ ልማት ባንክ ልዑካን ቡድን አባላት ጋር ውይይት አካሄደ





ከአፍሪካ ልማት ባንክ የመጡ የልዑካን ቡድን አባላት በፀረ-ሙስና ትግል ትብብር ዙሪያ ከፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ) እና ከሌሎች የኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎች ጋር ውይይት አካሂደዋል።

በውይይቱም በሀገር ደረጃ የፀረ-ሙስና ትግልን የሚያጠናክሩ የትብብር አጀንዳዎች በሰፊው ተዳስሰዋል፡፡

በመጨረሻም የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ ኮሚሽኑ ለሀገራዊ የፀረሙስና ትግል መጠናከር ከልማት ባንኩ ጋር በጋራ የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

# ኮሚሽኑ የመንግስት ባለሥልጣናት የሀብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ፕሮቶኮል ላይ ውይይት አደረገ







የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የፌደራል መንግስት ባለሥልጣናት የሀብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ሥነስርዓት ለማከናወን ከፌዴራል መንግስት ዘርፎች የሥነምግባር መከታተያ ሥራ አስፈጻሚዎች ጋር ግንዛቤ መስጫ ውይይት አድርጓል።

መድረኩ በዋናነት ለዘርፍ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና መከታተያ ሥራ አስፈጻሚዎች ግንዛቤን በመፍጠር ለአስመዝጋቢዎች ገለፃ እንዲያደርጉ ግልፅ ተልዕኮ የተሰጠ ሲሆን በፌደራል መንግስት አካላት ሥር የሚገኙ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እንዲሁም በቦርድ ለሚመሩ ከፍተኛ አመራሮች፤ በ2018 በጀት ዓመት ዘርፍ-ተኮር የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ-ግብር ተከናውኖ ሀብታቸውን የማሳወቅ እና የማስመዝገብ ኃላፊነት እንዲወጡ ያስችላል።

ይህም ሥነምግባራዊ አመራርነት ባህል ለመገንባት፣ በግልጽነት እና በተጠያቂነት መርህ ሕዝብና መንግስትን ለማገልገል አጋዥ መሣሪያ በመሆኑ ኮሚሽኑ በቀጣይ የመረጃ ተዓማኒነት ክትትል የማድረግ ኃላፊነት እንደሚወጡ ተገልጿል።

የሀብት ማሳወቅ እና ምዝገባ ስርአት ዘርፍ ተኮር የፀረ ሙስና ትግል እንዲኖር ከማድረግ ባሻገር ወጥ የሆነ አቋም እንዲኖር የሚያደርግ መሆኑ ተገልጿል።









# 2ኛው አገርዓቀፍ የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሰፐርቪዥን ፕሮግራም ተካሄደ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን 2ተኛ ዙር አገርዓቀፍ የኮሚሽኖች የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን አካሂዷል፡፡

በአገርዓቀፍ የኮሚሽኖች የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን መርሃግብር የፌደራሉን ጨምሮ ሁሉም የክልል እና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ተሳትፎ አድርገዋል፡፡

ድጋፋዊ ሱፐርቪዥኑ በዋናነት በ2017 በጀት ዓመት አገርዓቀፍ ኮሚሽኖች ያከናወኗቸውን የሥነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ሥራዎች እንዲሁም በ2018 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር፡፡

ኮሚሽኖች አገራዊ ተልዕኮ እንዲወጡ ለማድረግ ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ በሱፐርቪዥን ጊዜ ተቋማዊ አቅማቸውን መፈተሹ ነበር።

በተጨማሪም በሱፐርቪዥኑ በፀረ-ሙስና ተቋማት ያላቸውን አቅም እና ብቃት የሚያሳድጉ ጠንካራ የሪፎርም ሥራዎችን ጭምር ለማከናወን ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ከተለያዩ አካላት የተሰበሰቡበት ነው።

ባለፈው በጀት አመት የየኮሚሽኖች የተሰሩ ስራዎችን ላይ የታዩ መልካም ተሞክሮዎችን ለመለየት ትኩረት ለሚሹ ጉዳዮች በፌደራል፣ በክልል እና ከተማ አስተዳደር ኮሚሽኖች አቻ ለአቻ የድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ተከናውኗል፡፡

አገርዓቀፍ የኮሚሽኖች የአቻ ለአቻ ድጋፋዊ ሱፐርቪዥን ፕሮግራም ላይ የተሳተፉ የፌደራል፣ የክልል እና ከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት ለሥራው በተዘጋጀው ቼክ ሊስት እና የኮሚሽኑ የበላይ አመራሮች ማብራሪያና አቅጣጫ በሰጡት መሰረት ስራው ተከናውኗል፡፡

# አገራዊ የሙስና መከላከል ጥናትና ክትትል ዘርፍ የ2018 በጀት 1ኛ ሩብ አመት እቅድ አፈፃፀም በቨርቹዋል ተገመገመ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከክልል የስነምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽኖች ጋር የ2018 በጀት ዓመት የሙስና መከላከል ዘርፍን 1ኛ ሩብ አመት አፈፃፀም በቨርቹዋል ገምግሟል።

2018 በጀት ዓመት አፈፃፀም በፌደራል እና በክልል የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከሙስና መከላከል ዘርፍ አመራሮች ጋር በሙስና መከላከል ጥናት ፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል፣ በሀብት ምዝገባ እና የጥቅም ግጭት ባለፉት ሶስት ወራት የተከናወኑ ስራዎች ተገምግመዋል።

ግምገማው ክፍተቶችን በመለየት የምንማማርበት እና ተሞክሮዎችን የምንለዋወጥበት ነው ያሉት የሙስና መከላከል ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር አቶ እሸቴ አስፋው በቀጣይ በትኩረት በሚሰሩ ስራዎች ላይ አቅጣጫዎችን አስቀምጠዋል።









## የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ለኮሚሽኑ የእውቅና ሽልማት ሰጠ

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ለከተማው የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የእውቅና ሽልማት ሰጥቷል፡፡

ሽልማቱ ለምክር ቤቱ ተጠሪ የሆኑ ተቋማት የ2017 በጀት አመት ላይ ላሳዩት የላቀ አፈጻጸም የተሰጠ እውቅና መሆኑ ተነስቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ቡዜና አልከድር በ2017 በጀት አመት የላቀ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ተቋማት እውቅና መሰጠቱን ገልፀው በቀጣይም ምክር ቤቱ ለተቋማቱ እያደረገ ያለውን ክትትል እና ድጋፍ አጠናክሮ በማስቀጠል የላቀ አፈጻጸም እንዲኖራቸው ይደረጋል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር የስነ ምግብ እና የፀረ- ሙስና ኮሚሽን፣ ዋና ኦዲትና መስሪያ ቤት፣ የመሬት ማስለቀቅ እና ካሳ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚ ጉባኤ እና የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

## በመተሐራ ከተማ አምቡላንስ ሹፌር የኮንትሮባንድ እቃ ጭኖ በቁጥጥር ስር ዋለ

በኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ሸዋ ዞን መተሐራ ከተማ አንድ የአምቡላንስ ሹፌር ታማሚ ወደ ሕክምና ተቋም እያጓጓዘ በማስመሰል ሳይረን እያሰማ የፍተሻ ኬላ ለማለፍ ሲሞክር፣ የኮንትሮባንድ እቃ ጭኖ በፖሊስ ተይዟል። የመተሐራ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ እንደገለጸው፣ ከአንድ ነጥብ ሶስት (1.3) ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያለው የተለያዩ ዓይነት የሲጋራ ምርቶች በአምቡላንሱ ውስጥ ተገኝቷል።




የመተሐራ ከተማ ፖሊስ ፅህፈት ቤት ሃላፊ ኢንስፔክተር ሽፈራው መለሰ እንደገለጹት፣ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 4 01299 አፋር የሆነ ይህ አምቡላንስ፣ ለጤና ተቋማት አገልግሎት የተመደበ ሲሆን፣ ከአፋር አዋሽ ከተማ ወደ አዳማ ከተማ ታማሚ እያጓጓዝሁ ነው በማለት የፍተሻ ኬላ ለማለፍ ሞክሯል። ሆኖም፣ በቆርኬ የፍተሻ ጣቢያ በተደረገ ፍተሻ ወቅት ከ1.3 ሚሊዮን ብር በላይ ዋጋ ያለው የኮንትሮባንድ እቃ ተገኝቷል።

ሹፌሩ ተጨባጭነት ለመስጠት፣ የሕክምና ባለሙያ ጋዋን የለበሰ ሰው ከጎኑ አስቀምጦ ታማሚ እንዳለ ለማስመሰል ሞክሯል። የፍተሻ ጣቢያው ፖሊሶች በመጠራጠር ተሽከርካሪውን መርምረው የኮንትሮባንድ እቃውን በቁጥጥር ስር አውለዋል።

ኢንስፔክተር ሽፈራው መለሰ እንደገለጹት፣ መንግስት ለታማሚዎችና ለወላድ እናቶች አገልግሎት በከፍተኛ ወጪ ያስገባቸው አምቡላንሶች ለሌላ ዓላማ መጠቀማቸው ትልቅ ወንጀል ነው። በሹፌሩና በተባባሪው ላይ በቂ ማስረጃ መገኘቱን ገልጸው፣ ለፍትሕ እንደሚቀርቡ አስታውቀዋል።

## ከባንኮች ከፍተኛ ድርሻ የሚገዙ አካላት የገንዘባቸውን ምንጭ እንዲያሳውቁ የሚያስገድድ ረቂቅ መመሪያ ተዘጋጀ

ብሄራዊ ባንክ፣ የባንኮችን ከፍ ያለ መጠን ያላቸው የአክሲዮን ዝውውሮች ለመቆጣጠር ወይም ለማገድ ሥልጣን የሚሠጠውን ረቂቅ መመሪያ ማዘጋጀቱን አስታውቋል።

ረቂቅ መመሪያው፣ ከባንኮች ከፍተኛ ድርሻ የሚገዙ አካላት የገንዘባቸውን ምንጭ እንዲያሳውቁ የሚያስገድድ ነው። አ

መመሪያው፣ የአክሲዮን ዝውውሮች ግልጽና ዓለማቀፍ መስፈርቶችን ባሟላ መልኩ እንዲካሄዱ ለማረጋገጥ ያስችላል ተብሏል።

# የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት

# NCRS

# ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!

# የአዲስ አበባ ፖሊስ ሀሰተኛ ሰነዶችን አዘጋጅ የነበሩ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር አዋለ







የአዲስ አበባ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ በቦሌና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተሞች ውስጥ ሀሰተኛ ማህተሞችና ቲተሮችን በመጠቀም ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጁ የነበሩ ተጠርጣሪዎችን በቁጥጥር ስር ማዋሉን አስታውቋል።

በቦሌ ቡልቡላ 40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት ውስጥ የተካሄደው ብርበራ አላዛር ሠለሞን የተባለ ተጠርጣሪን በቁጥጥር ስር አውሏል። ፖሊስ በተጠርጣሪው ባደረገው ብርበራ ተከራይቶ በሚኖርበት ቤት ውስጥ የተለያዩ የመንግስትና የግል ተቋማት ሀሰተኛ ማህተሞችና ቲተሮችን በመጠቀም ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጅ መኖሩን መረጃ በማግኘት ተንቀሳቅሷል። በዚህ ብርበራ ወደ 50 የሚጠጉ ማህተሞችና ቲተሮች፣ ኮምፒውተር፣ ፕሪንተር እና ሌሎች ቁሳቁሶች ተይዘዋል። ከተያዙት ሰነዶች መካከል የኤሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳዮች መስሪያ ቤት፣ የአዋሽና የንብ ኢንተርናሽናል ባንኮች፣ እንዲሁም የክልልና የዞን አስተዳደር ሰነዶች ይገኙበታል። ተጠርጣሪው በኤግዚቢትነት ተይዞ ምርመራ እየተካሄደ ነው ብሏል ፖሊስ።

በተመሳሳይ የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በወረዳ 4 ዓለም ባንክ አካባቢ በተካሄደ ክትትል አራት ተጠርጣሪዎችን - ዘሪሁን ገ/ማርያም፣ ምንተስኖት ለማ፣ ፀጋዬ ጋዲሳ እና በአንተ አምላክ ግርማን በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ሀሰተኛ ሰነዶችን ሲያዘጋጁ በቁጥጥር ስር አውሏል። ከዚህ በተጨማሪ ከወንጀሉ ጋር ተያይዘው አብረሐም ጋዲሳ፣ ታጋይ ታደስ፣ መንገሻ ሺመልስ፣ ገ/ማርያም አመርጋ፣ ሚፍታ ጁሀር፣ ዩሀንስ ተስፋዬ፣ ገነት ዋለልኝ፣ ይታገሱ አያሌው እና ፈሪዲሳ መገርሳ ተጠርጥረው ተይዘዋል በማለት ገልጧል።

ፖሊስ እንደገለጸው፣ በዚህ ብርበራ ከተያዙት ሰነዶች መካከል የአስራ አንዱ ወረዳዎች፣ የአዲስ ከተማ ወረዳ 13፣ የጉለሌ ወረዳ 5፣ የንፋስ ስልክ ላፍቶ ወረዳ 1ና 2፣ የሸገር ከተማ ፉሪ ወረዳ 2፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የስልጤ ዞን ክብ ማህተሞች፣ የልደት ካርዶች፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ማስረጃዎች፣ የሰነዶች ማረጋገጫ ሰነዶች፣ እንዲሁም ሀሰተኛ ሰነዶችን ለማዘጋጀት የተጠቀሙባቸው ሁለት ፕሪንተሮች፣ ሁለት ኮምፒውተሮች፣ አንድ ላፕቶፕ እና ሦስት የመታወቂያ መቁረጫ መሣሪያዎች በኤግዚቢትነት ተይዘዋል።

የተጠርጣሪዎች ምርመራ በቀጣይነት እየተካሄደ ሲሆን፣ ፖሊስ ተጨማሪ መረጃዎችን እንደሚያሳውቅ ቃል ገብቷል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ ጠቅላይ መምሪያ መኖሪያ ቤት የሚያከራዩ ግለሰቦች የተከራዮችን ማንነት የማጣራትና የማረጋገጥ ግዴታ እንዳለባቸው አሳስቧል። በተጨማሪም፣ ህገወጥ ተግባራትን ለመከላከል ህብረተሰቡ ጥቆማ በመስጠት እና እንደዚህ ያሉ ተግባራትን በማጋለጥ ያለውን ተሳትፎ ማጠናከር እንደሚገባ አፅንኦት ሰጥቷል።

## የሥነምግባር ጥሰት በፈፀሙ 20 አመራርና ሰራተኞች ላይ እርምጃ ተወሰደ- አገልግሎቱ

ባለፉት ሶስት ወራት በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የዲጂታል የሙስና መረጃ (ጥቆማ) መቀበያ ስርዓት እና ሌሎች አማራጮች በቀረቡት ጥቆማዎች መሰረት 20 አመራሮችና ሰራተኞች ላይ እርምጃ መወሰዱን ገለጸ::


ተቋሙ ተግባራዊ ባደረገው የዲጂታል ሙስና ጥቆማ መቀበያ ስርዓት እና ሌሎች አማራጮች በቀረቡት ጥቆማዎች መሰረት በሩብ ዓመቱ እርምጃ ከተወሰደባቸው ሰራተኞች መካከል 8 የፅሁፍ፣ 10 የደመወዝ፣ 2 ስንብት በድምሩ 20 አመራሮችና ሰራተኞች ላይ እርምጃ መወሰዱን በፌስቡክ ገፁ አሳውቋል::

በዲጂታል ሙስና ጥቆማ መቀበያ ስርዓት እና ሌሎች አማራጮች 170 ጥቆማዎች/ አቤቱታዎች ቀርበው ከነዚህ ውስጥ 152 ጥቆማዎችና አቤቱታዎች ተጣርተው ተግባራዊ መደረጋቸውን አስታውቋል::

በሩብ ዓመቱ የብልሹ አሰራር ጥቆማ ከቀረበባቸው የሥራ ሂደቶች መካከል የአዲስ ኃይል ጥያቄ፣ የኃይል መቆራረጥና አስቸኳይ ጥገና፣ የቆጣሪ ንባብና የቢል ስብሰባ፣ ከንብረት አያያዝና አጠቃቀም ጋር የተያያዙ እንዲሁም ሌሎች ልዩ ጉዳዮች ይገኙበታል::

በ2018 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሶስት ወራት የቀረቡ ጥቆማዎች ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀሩ በ179 በመቶ ጭማሪ እንዳሳዩ ተገልጿል፤ ይህም የዲጂታል የጥቆማ መቀበያ ስርዓት መተግበሪያ ያመጣውን ምቹ ሁኔታ ያመለክታል ተብሏል::

ተቋሙ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችንና ብልሹ አሰራሮችን ለመታገል እና እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኝነቱን እንደሚቀጥል ገልጿል:: በተጨማሪም ተገልጋዩ ማህበረሰብ መሰል ችግሮችን ሲመለከት በተዘረጋው ዘመናዊ የሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ወይም ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ ጥሪ አቅርቧል::



ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ


ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission


**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**

**EARS**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች


ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1


**NCRS**



# ርዕሰ -አንቀፅ

## ቴክኖሎጂን ለሙስና መከላከል!

ቴክኖሎጂ ሙስናን ለመከላከል የሚኖረው ጥቅም በጣም ጉልህ ነው። ቴክኖሎጂ በዘመናዊው ዓለም ውስጥ ሙስናን ለመከላከል እና ለመቀነስ ወሳኝ መሣሪያ ነው፡፡ እንደ ብሎክቼይን፣ ሰው ሰራሽ አስተውሎት(AI) እና የመረጃ ትንታኔ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ግልፅነትን በመጨመር፣ የገንዘብ ፍሰቶችን በመከታተል እና ያልተለመዱ እንቅስቃሴዎችን በመለየት ሙስናን ለመግታት እጅግ ውጤታማ መንገዶችን ይሰጣሉ። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገሮች፣ ሙስና የኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ እድገትን የሚገታ ችግር ስለሆነ፣ ቴክኖሎጂን መጠቀም የተቋማትን ተጠያቂነት እና ቅልጥፍና ለማሻሻል ወሳኝ ነው።

ከዚህም በላይ፣ ቴክኖሎጂ ሙስናን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን ዜጎች በቀጥታ ተሳታፊ እንዲሆኑ እድል ይሰጣል። ለምሳሌ፣ የመስመር ላይ ቅሬታ መድረኮች እና የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ሥርዓቶች ሰዎች ሙስናን በሚስጢር ሪፖርት እንዲያደርጉ እና የገንዘብ ግብይቶችን በቀላሉ እንዲከታተሉ ያስችላሉ።

ዋና ዋና ጥቅሞቹን እንመልከት፡

ግልፅነት መጨመር፡ ቴክኖሎጂ፣ በተለይ የዲጅታል ግብይት ሁሉም ግብይቶች በዲጂታል መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገቡ እና እንዳይቀየሩ ያደርጋል። ይህ ማለት ማንም ሰው መረጃውን ሳያስታውቅ መቀየር አይችልም፣ ይህም የሙስና እድልን ይቀንሳል። ምሳሌ፡ በኢትዮጵያ የመንግሥት ግዥ ሥርዓቶች ውስጥ ብሎክቼይን በመጠቀም የጨረታ ሂደቶች ግልፅ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ኩባንያዎች የጨረታ ሰነዶችን በብሎክቼይን ላይ መዝግበው ማንም ሰው ሰነዶቹን መቀየር እንዳይችል ማድረግ ይቻላል። ይህ በጨረታ ሂደት ውስጥ ሙስናን ይቀንሳል። ክትትል እና ቁጥጥር፡ የመረጃ ትንታኔ እና ሰው ሰራሽ አስተውሎት(AI) ያልተለመዱ እንቅስቃሴዎችን በፍጥነት መለየት ይችላሉ። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በተለመደ የገንዘብ ፍሰቶች ውስጥ ያልተለመዱ ነገሮችን በመለየት ሙስናን ያስቀራሉ። ምሳሌ፡ በባንኮች ውስጥ የሰው ሰራሽ አስተውሎት ሥርዓቶች ያልተለመዱ የገንዘብ ማስተላለፎችን ይተነትናሉ። ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ የንግድ ባንክ ያልተለመደ ትልቅ የገንዘብ ማስተላለፍ በሰው ሰራሽ አስተውሎት ተለይቶ ለተጨማሪ ምርመራ ሊቀርብ ይችላል። ይህ የገንዘብ ማጭበርበርን ወይም ሌላ ሙስናን መከላከል ይችላል።

የዲጂታል ሰነድ አስተዳደር፡ ዲጂታል ሰነዶችን መጠቀም የወረቀት ሥራዎችን በመቀነስ፣ መረጃዎች እንዳይጠፉ ወይም እንዳይቀየሩ ያደርጋል። ይህ በተለይ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ የሙስና እድልን ይቀንሳል። ምሳሌ፡ በኢትዮጵያ የመሬት ባለቤትነት ምዝገባ ሥርዓት ውስጥ ዲጂታል ስርዓቶችን በመጠቀም የመሬት ሰነዶች በኤሌክትሮኒክ መልክ መቀመጥ ይችላሉ። ይህ የመሬት ማጭበርበርን ወይም የሰነድ ማጭበርበርን ይከላከላል።

የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ስርዓቶች፡ የኤሌክትሮኒክ ክፍያዎች የገንዘብ ፍሰትን መከታተል ቀላል ያደርጉታል። የጥሬ ገንዘብ አጠቃቀም ለሙስና ተስማሚ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም መከታተል ከባድ ነው። ዲጂታል ክፍያዎች ግን ሁሉም ግብይቶች መዝግበው ይቀመጣሉ። ምሳሌ፡ በኢትዮጵያ የቴሌብር እና ሌሎች የሞባይል ክፍያ መድረኮች መስፋፋት የጥሬ ገንዘብ አጠቃቀምን በመቀነስ የሙስና እድልን ይገድባል። ለምሳሌ፣ የመንግሥት አገልግሎቶች ክፍያዎች በዲጂታል መንገድ መፈፀም ሙስናን ይቀንሳል። የዲጂታል ሪፖርት ማድረግ እና ቅሬታ ፡ የመስመር ላይ መድረኮች ሰዎች ሙስናን በስውር እና በደህና መልኩ ሪፖርት እንዲያደርጉ ያስችላሉ። ይህ በተለይ በሙስና ምክንያት ቅጣት ወይም ማስፈራሪያ ለሚፈሩ ሰዎች ጠቃሚ ነው። ምሳሌ፡ በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የመስመር ላይ ቅሬታ መድረክ በመፍጠር ዜጎች ስለ ሙስና መረጃ በቀላሉ ማቅረብ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ የስልክ መተግበሪያ በመጠቀም ሰዎች ስም-አልባ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

የኦንላይን ሰራተኞች ሥልጠና ማብራሪያ፡ የኦንላይን ላይ ሥልጠና መድረኮች ሰራተኞች ስለ ሙስና መከላከል እና ስለ ሥነ ምግባር ትምህርት እንዲያገኙ ያግዛሉ። ይህ በተለይ በመንግሥት እና በግል ተቋማት ውስጥ ያሉ ሰራተኞችን ለማስተማር ይረዳል። ምሳሌ፡ የመንግሥት ተቋማት ሰራተኞቻቸውን ለማሰልጠን የመስመር ላይ ኮርሶችን መጠቀም ይችላሉ። ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሰራተኞችን ስለ ሙስና መከላከል ለማስተማር የኢ-ማኅበረሰብ መድረኮችን መጠቀም ይችላል።

በአጠቃላይ ቴክኖሎጂ ብቻውን ሙሉ መፍትሔ አይደለም። ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የኢንተርኔት መዳረሻ ውስንነት፣ የቴክኖሎጂ እውቀት እጥረት ወይም የህግ አፈፃፀም ድክመቶች ፈተናዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህ፣ ቴክኖሎጂ ከጠንካራ የህግ ማዕቀፎች፣ የህዝብ ግንዛቤ እና የተቋማት ቁርጠኝነት ጋር ተዳምሮ መጠቀም አለበት የሚል መልዕክት አናስተላልፋለን።

# ቆይታ



# መሶብ የአንድ ማዕከል አገልገሎት ለሙስና መከላከል!

የፌደራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተልዕኮውን ለመፈጸም የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል:: ከእነዚህ መንገዶች አንዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሲሆን፣ በዚህም በየሁለት ሳምንቱ አንድ ጊዜ የሚዘጋጅ የዲጂታል ጋዜጣ በማዘጋጀት ለማኅበረሰቡ ያደርሳል:: ጋዜጣው ከያዛቸው አምዶች መካከል ቆይታ አንዱ ነው:: በዚህ ዝግጅት ቆይታ ያደረገነው በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና መከላከል ጥናት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ገዛኸኝ ጋሻው ጋር አጭር ቃለ መጠይቅ አካሂደናል:: በዚህ ቃለ መጠይቅ መሶብ የአንድ ማዐከል አገልግሎት ሙስናና ብልሹ አሠራርን ከመከላከል አኳያ ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-



**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** የመሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ምንድን ነው? አላማውስ?

**አቶ ገዛኀኝ ጋሻው፡-** የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት በአንድ ቦታ ዜጎች አገልግሎት ለማግኘት የተለያዩ ቦታዎችን መጎብኘት ሳይጠበቅባቸው፣ ከእንግልትና ከተለያዩ ችግሮች ነፃ በሆነ መልኩ፣ በአንድ ማዕከል ተደራጅቶ ቀልጣፋ እና ከብልሹ አሰራር ነፃ የሆኑ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል ዘዴ ነው::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** እንደ ሀገር የፀረ-ሙስና ትግል ጀምረናል:: መሶብ የአንድ ማዕከል አገልግሎት የፀረ-ሙስና ትግሉን ከማስቀጠል እና ውጤት ከማምጣት አንፃር ምን ያህል እገዛ ያደርጋል ይላሉ?

**አቶ ገዛኀኝ ጋሻው፡-** ሙስና ተለዋዋጭ ባህሪ አለው:: ተለዋዋጭ ባህሪ ያለው ሙስና አሰራሩን በየጊዜው እያዘመነ እና እየቀያየረ መሄድ ይኖርበታል:: ስለዚህ፣ ከዚህ ተለዋዋጭ ባህሪ ጋር አብሮ መሄድ ካልተቻለ፣ ዜጎች ለእንግልት ይጋለጣሉ፣ ወይም አሰራሩን በፍጥነትና በተፈለገው ጥራት መፈጸም አይቻልም:: ስለዚህ፣ ብልሹ አሰራርና ሙስናን ለመከላከል እንደ መሶብ ያሉ ስርዓቶች መዘርጋታቸው እጅግ ጉልህ ሚና ይጫወታል:: ኢትዮጵያ የአለም አቀፉን የፀረ-ሙስና ስምምነት እና የአፍሪካ የሙስና መከላከልና መዋጋት ኮንቬንሽኖችን ፈርማ አጽድቃለች፣ እነዚህንም የሀገሪቱ ህግ አካል አድርጋለች:: ከዚህ አንፃር፣ አሰራሮችን ዘመናዊ ማድረግ፣ ማደራጀት እና ከዘመኑ ጋር መላመድ ከሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱ ነው:: ይህን መሰረት በማድረግ፣ የመሶብ አገልግሎት በመተግበር ብልሹ አሰራርን መከላከል፣ ጊዜውን የጠበቀ አገልግሎት መስጠት እና ውጤታማ ስርዓት መዘርጋት ይቻላል::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** መሶብ የአንድ ማዕከል በቴክኖሎጂ የታገዘና ባለጉዳዮች ጉዳያቸውን በአንድ ቦታ እንዲጨርሱ የሚያስችል ስርዓት ነው:: በአገልግሎት ሰጪ ተቋማትና በተገልጋዮች መካከል ያለውን ግንኙነት ጤናማ ማድረግ ላይ ምን ድርሻ ይኖረዋል ይላሉ?

**አቶ ገዛኀኝ ጋሻው፡-** አገልግሎት ፈላጊ ወደ አንድ ተቋም ሲሄድ ሁለት ተዋናዮች አሉ፡ አገልግሎት ሰጪው አካል (የመንግስት ተቋም) እና አገልግሎት ፈላጊው ዜጋ:: በዚህ መካከል ያለው መብትና ግዴታ ግልፅ መሆን አለበት:: የመሶብ አገልግሎት ይህን መብትና ግዴታ በግልፅ ይደነግጋል:: ተገልጋዩ ወደ መሶብ ሲመጣ፣ ምን ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላት እንዳለበት በስርዓቱ ተቀምጦ ይገለጻል፣ ይህም አላስፈላጊ ግንኙነቶችንና ብልሹ አሰራሮችን ይቀንሳል:: ስርዓቱ መብትና ግዴታዎችን በግልፅ በማስቀመጥ፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ያረጋግጣል:: አገልግሎት ሰጪው በተቀመጡ መስፈርቶች መሰረት ካልሰራ፣ ተጠያቂ ይሆናል፣ ተገልጋዩም መስፈርቶችን ሳያሟላ አገልግሎት ማግኘት እንደማይችል ያውቃል:: ይህ ሁለቱን ተዋናዮች በጤናማ መንገድ ያስተሳስራል፣ ይህም የአሰራሩን ቅልጥፍና እና ግልጽነት ያረጋግጣል::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** እንደ መሶብ አገልግሎት ያሉ ስርዓቶችን ከመጀመር ባሻገር ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ምን አይነት ክትትል መደረግ አለበት ይላሉ?

**አቶ ገዛኀኝ ጋሻው፡-** እንደዚህ አይነት ስርዓቶች መጀመራቸው ትልቅ እርምጃ ነው፣ ነገር ግን ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ የክትትልና የቁጥጥር ስልቶች መጠቀም አለባቸው:: ተቋማት ተጠያቂ እንዲሆኑ፣ ስርዓቱ በየጊዜው እየተሻሻለና እየተጠናከረ መሄድ አለበት:: ይህም ማለት፣ ስርዓቱን ማሳደግ፣ ውጤታማነቱን መገምገም እና በየጊዜው ድጋፍና ግብረ መልስ በመስጠት ማጠናከር ያስፈልጋል::

**ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-** በሌሎች መስኮችም ጊዜውን የጠበቀ የሙስና መከላከልና የሀገር ሀብትን የመጠበቅ አስተዋፅኦ ለማበርከት አዳዲስ አሰራሮችን መተግበር ላይ ምን አይነት ስራዎች መሰራት አለባቸው ይላሉ?

**አቶ ገዛኀኝ ጋሻው፡-** ተቋማት እንደ መሶብ አገልግሎት ያሉ ስርዓቶችን በማዕከል በማቀናጀት መስራት አለባቸው:: እንደ ነባራዊ ሁኔታቸውና ሀላፊነታቸው፣ አሰራሮቻቸውን ከወረቀት ነክ ሥራ ነፃ በማድረግ ዲጂታል ስርዓቶችን በማበልፀግ መተግበር አለባቸው:: ለምሳሌ፣ በፌዴራል ደረጃም ሆነ በክልል ደረጃ፣ ከወረቀት ነክ ሥራ ነፃ የሆኑ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ተቋማት አሉ:: ለምሳሌ፣ በፌዴራል የሥነ ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ያሉ የጥቆማ መስጫ ስርዓቶች፣ ብሄራዊ የሙስና ጥቆማ ስርዓት (NCRS) እና ዲጂታል የሀብት ምዝገባና ማሳወቂያ ስርዓት (EARS) እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ:: እነዚህን ስርዓቶች በማበልፀግና በማዘመን፣ ከወረቀት ነክ ሥራ ነፃ በማድረግ እና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ፣ ተቋማት ከተሰጣቸው ሀላፊነት ጋር ተጣጥመው እንዲህ ያሉ ስርዓቶችን መተግበር አለባቸው:: ይህ እንደ መሶብ ያሉ ስርዓቶችን ውጤታማ ያደርጋል፣ ብልሹ አሰራሮችን ይፈታል፣ እንግልቶችን ይቀንሳል እና የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ያሻሽላል::

አመሰግናለሁ!

# ኪነ-ጥበብ

## ማነው ተጠያቂ?

ስብዕና ለሌለው ከመስመር ለወጣ፤
አደራውን በልቶ ሀሰትን ለጠጣ፤
ምግባርን አጉድሎ ራሱን ለቀጣ፤
እምነት ላጎደለ ማንነቱን ላጣ፤
ማነው ተጠያቂ ሰው ምግባሩን ታጣ፡፡

ህጻናት፣ ወጣቱ ብሎም አዛውንቱ፤
ማመን መታመንን ካደረገው ከንቱ፤
ማጭበርበር፣ ማታለል ሲሆን ማንነቱ፤
ሀሰትን ተላምዶ ከጠፋው እውነቱ፤
ማን ከፍርድ ይቁም የማን ነው ጥፋቱ?

ማነው ተጠያቂ ?
ወላጅ አሳዳጊ፤ እናት፣ አባት፣ እህት፤
ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ የቅርብ ጎረቤት፤
መምህር አስተማሪ ወይስ ት/ቤት፤
ኡዝታዝና ፓስተር፣ መምራን ቄሳውስት፤
ባህልና ልማድ እሴት ነው ሀይማኖት፤
ማነው ወንጀለኛ ይቁም ከዳኛ ፊት፡

ግን እኔ እሚመስለኝ ስዳኛው እራሴ፤
መጽሃፍ ላይ ካየሁት ሳነብም ከዶሴ፤
ለትውልድ ግንባታ ሁሉም ተጠያቂ ፍርደኛ ነው
መልሴ፡፡

እናም ተጠያቂ ሁላችን ባንድነት፤
ትውልድን እንገባ ከስር ከልጅነት፤
በጥሩ ምሳሌ ሆነን አርዓያነት፤
መልካም ምግባር ይሁን የሰው ልጅ ማንነት፤
ሀገር እድትለማ እንድታድግ በእውነት፡፡

ከያብባል አዲስ

# ሳይቃጠል በቅጠል

## የሥራ አመራር ቦርድ ድርሻ እና የጥቅም ግጭት ተጋላጭነት፤

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ተቋማዊ ኃላፊነትን መነሻ በማድረግ ከሀገር፣ ከህዝብ ወይም ከተቋም ጥቅም ይልቅ የግልን፣ የቤተሰብን እና የቅርብ ዘመድን የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅምን ለማስቀደም የሚያስችል ሂደት ነው፡፡ ሂደቱ በተለይ ውሳኔ በሚያሳልፉ አካላት የሚፈፀም ከሆነ በተቋማት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ከፍተኛ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የጥቅም ግጭት ሂደት የሙስና ወንጀል ከመሆኑ በፊት መከላከል እንዲቻል ሀገራችን ተቀብላ ባፀደቀችው የተባበሩት መንግስታት የፀረ-ሙስና ስምምነት እና በሌሎች ህጎች ውስጥ በግልፅ ተመላክቷል፡፡

የጥቅም ግጭት በአብዛኛው በመንግስት ተቋማት እና ህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ የኃላፊነት ድርሻ ካላቸው አመራሮች፣ የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ጋር ይያያዛል፡፡ በዚህ ረገድ የሥራ አመራር ቦርድ የሥራ ድርሻ ወይም ኃላፊነት በአግባቡ ካልተመራ ለጥቅም ግጭት ተጋላጭነቱ ከፍተኛ ከመሆኑም በተጨማሪ ለሙስና ወንጀል መፈፀም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

የሥራ አመራር ቦርድ አባላት በተቋማት ላይ ድርሻቸውን ሲወጡ ለጥቅም ግጭት ያላቸውን ተጋላጭነት ከማስቀረት አንፃር የሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት የሚሹ ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

- የሥራ አመራር ቦርድ ስትራቴጂክ አመራር ከመስጠት፣ የቁጥጥርና ክትትል እንዲሁም የድጋፍና ማማከር ሥራዎች ከማከናወን አንፃር የአንድ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅቶች የልማት ተቋም የበላይ አካል በመሆኑ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ግልጽ፣ አሳታፊ እና ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ሂደቶች ሁሉ ከጥቅም ግጭት ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤

- አንድ የተቋም ኃላፊ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ሆኖ ድርሻውን ሲወጣ ለተለያዩ የጥቅም ግጭቶች ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ለአብነትም፡ - አመራሩ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚመራው ወይም በሚቆጣጠረው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የልማት ተቋም ላይ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ከሆነ እንደ አንድ የዘርፉ ወይም የተቋሙ የበላይ ኃላፊ አዋጅ እና ደንብ ለማስፈፀም ያወጣቸውን ወይም የሚያወጣቸውን መመሪያዎች እና የአሠራር ስታንዳርዶች ግልፅ የቁጥጥር ሥርዓት (Check and balance) ሳይኖር ሥራዎችን እንዲሰራ ሁኔታዎች ሊያስገድዱት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም አንድ የተቋም አመራር ወይም ኃላፊ በሚመራው ወይም በሚቆጣጠረው ተቋም ሥር ባሉ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የልማት ተቋማት ላይ በሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢነት ወይም አባልነት ሊሳተፍ አይገባም፤

- የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ሆኖ የሚሾም አመራር ወይም የሥራ ኃላፊ የቦርድ ድርሻውን ከሚወጣበት ተቋም ጋር የግዥ አቅራቢነት እና የተለያዩ ፕሮጀክቶች ግዥ ተሳታፊነት ሚና፣ የቅርብ ቤተሰብን በተቋሙ እንዲቀጠሩ፣ እንዲመደቡ ወይም እንዲሾሙ የማድረግ ሚና እና ሌሎች ለጥቅም ግጭት የሚዳርጉ ሥራዎችን ከማከናወን ሊቆጠብ ይገባል፤

- የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ወይም አባል ሆኖ የሚሾም አመራር ወይም የሥራ ኃላፊ በጥቅም ግጭት ውስጥ ሲገባ ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ራሱን ማግለል ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በሰው ሀይል ቅጥር፣ ምደባ እና ሹመት ሂደት ላይ ከሰዎች ወይም ከተቋማት ጋር ያለውን የግል ግንኙነት ለሚሰራበት ወይም አግባብነት ላለው ተቋም ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

- በመሆኑም የሥራ አመራር ቦርድ ድርሻን ከመወጣት አኳያ የሚያጋጥሙ የጥቅም ግጭቶች በአውንታዊነት መከላከል እና ማስወገድ ያስፈልጋል። ነገር ግን በየጊዜው የሚያጋጥሙ የጥቅም ግጭቶችን በወቅቱ አለመከላከል የሙስና ወንጀል እንዲንሰራፋ ሰፊ ዕድል ይፈጥራል፡፡ ይህም የሙስና ወንጀሎችን ለመደንገግ በወጣ አዋጅ ቁጥር 881/2007 መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል፡፡

# መልካም ዜጋ

## የወላጇን ህይወት ለመታደግ መልካም ተግባር የፈፀመ የአንቡላንስ ሹፌር





የአምቡላንስ ሹፌር ሀብታሙ ደርጉ በጎፋ ዞን መሎ ጋዳ አካባቢ አንዲት ወላድ እናትን ወደ ሆስፒታል ለመውሰድ በአምቡላንስ ሲጓዝ፣ በጃውላ መንገድ ተብሎ በሚጠራው ቦታ፣ ከሌሊቱ 8 ሰዓት አካባቢ አምቡላንሱ በጭቃ ተጠመደ:: ሀብታሙ እና ከእሱ ጋር የነበሩ ሰዎች መኪናውን ለማውጣት መሞከር ቢጀምሩም፣ ጥረታቸው አልተሳካም:: በዚህ ጊዜ ወላዷ በቦታው ላይ ወለደች፣ ነገር ግን አሳዛኝ ሆኖ፣ የተወለደው ህፃን ሞቷል::

ሀብታሙ የእናትየዋን ህይወት ለመታደግ መኪናውን ለማላቀቅ ብዙ ጊዜ ቆፍሮ መሞከሩን ገልፆ፣ ከተሰማው ጭንቀትና ድካም የተነሳ በጭቃው አጠገብ ቁጭ ብሎ እንዳለቀሰ ይናገራል:: የወላጇን ስቃይ ማየት ባለመቻሉ እንባዋን ባየ ጊዜ እሱም ተቆጥሮ እንዳለቀሰ ገልፆ፣ ይህ ሁሉ ጥረት ህፃኑን ማዳን ባለመቻሉ በጣም እንዳዘነ አክሏል::

በመቀጠል ሀብታሙ ለሃላፊው ደውሎ ስለተፈጠረው ሁኔታ ነግሮታል:: እናትየው የደም ካንሰር ስላለባት በህይወት ለመቆየት ወደ ሆስፒታል መድረስ እንዳለባት አሳውቋል:: በመቀጠል ከቡልቄ ወረዳ ሌላ አምቡላንስ መጥቶ እናትየውን ወደ ሆስፒታል ወሰዳት:: ከዚያ በኋላ እናትየው ወደ ጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል ለህክምና ተመራች፣ ነገር ግን ለህክምናው የሚያስፈልገው 800,000 ብር ስለተጠየቀ፣ አሁንም እርዳታ እየተሰበሰበ ነው::

ሀብታሙ በአምቡላንስ ሹፌርነት ለሁለት አመታት ሲያገለግል የቆየ ሲሆን፣ ተመሳሳይ ችግሮች በተለይ መንገዶች ላይ በተደጋጋሚ እንደሚገጥሙት ገልፆ፣ አንዳንዴ ሁለት እና ሶስት ቀናት መንገድ ላይ መቆየት እንደነበረበት አስታውሷል::